ብሉይ ኪዳን

ክፍለ ትምህርት 1

መግቢያ ጥያቄዎች

1. ተማሪ ዎች የአዳም እና ሄዋን ልጆች ማን ናቸው?
2. መርከብ ታውቃላችሁ? ጥቅሙ ምንድን ነው?

አቤል እና ቃየል

አዳም እና ሄዋን የመጀመሪያ ልጅ ቃየል ነው። አቤል ሁለተኛ ልጅ ነው። አቤል በግ ጠባቂ ነበር። ቃየልም ምድርን የሚያርስ ነበር። ከብዙ ቀን በኋላ ቃየል ከምድር ፍሬ ለእግዚአብሔር መስዋዕት አቀረበ። አቤልም ከበጎቹ የሰባውን መጀመርያ የተወለደውን አቀረበ።

እግዚአብሔርም ወደ አቤልና መስዋዕቱ ተመለከተ። ወደ ቃየልና ወደ መስዋዕቱ ግን አልተመለከተም።ቃየልም ፊቱ ጠቆረ።

እግዚአብሔርም ለምን ፊቱ እንደጠቆረ ጠየቀው። ጥሩ መስዋዕት እንዳላቀረበም ነገረው። ቃየልም በዚህ ተናዶ ወንድሙ አቤልን ና ወደ ሜዳ እንሂድ አለው።ቃየልም በወንድሙ በአቤል ላይ ተነሳበት ገደለውም።

እግዚአብሔር ቃየልን ወንድምህ አቤል ወዴት ነው? አለው። ቃየልም አላውቅም እኔ የወንድሜ ጠባቂ ነኝን? አለ። እግዚአብሔርም ስለ አቤል ቃየልን ረገመው ቃየልን ያገኘው ሁሉ እንዳይገድለው ምልክት አደረገበት።

ኖህ

ኖህ የሚባል አንድ ደግ እና ፃድቅ ሠው በአንድ ሀገር ውስጥ ይኖር ነበር። እግዚአብሔርም ኖህን መርከብ እንዲሠራ አዘዘው። ኖህም መርከቡን በሚሠራበት ጊዜ የዚያ ሀገር ሠዎች ይስቁበት ነበር። ከዚያም ኖህ መርከቡን ሠርቶ ጨረሠ። በዚያን ወቅትም ከእያንዳንዱ ፍጥረት አንድ ወንድ እና ሴት እያረገ ወደ መርከቡ አስገባ። አስገብቶ እንደ ጨረሠም ከባድ ዝናብ መዝነብ ጀመረ። ዝናቡም ለ 40 ቀን ያህል ያለ ማቋረጥ ዘነበ። ከመርከቡ ውጭ ያሉ ሠዎችም በዝናቡ ምክንያት በተነሣው ጎርፍ ተውጠው ሞቱ። ኖህም የጥፋት ውሃ በምድር ላይ በሆነ ጊዜ የ 600 ዓመት ዕድሜ ነበር።

ኖህም ዝናቡ ማባራቱን ለማወቅ እንዲሁም ውሃው መውረዱን ለማጣራት ቁራን ላከው። ቁራው ግን ከተላከበት ሳይመለስ ቀረ። ከዚያም ርግብን እንድታጣራ ላካት። እሷው ውሃው መውረዱን የሚያመለክት የወይራ ቅጠል ይዛ መጣች። ከዚያው በመርከቡ ውስጥ የነበሩ ፍጥረታት በሙሉ ከመርከቡ ወረዱ።

መልመጃ

1. አቤል ና ቃየል የማን ልጆች ነበሩ?
2. አቤል ላቀረበው መስዋዕት እግዚአብሄር ምን አደረገለት?
3. ቃየን አቤልን በመግደሉ ምን ሆነ?

4. ኖህን መርከብ እንዲሰራ ያዘዘው ማን ነው?
5. መርከቡ ውስጥ የገቡት እነማን ናቸው?
6. በተላከበት ሄዶ የቀረው ማን ነው?
7. ርግብ ምን ይዛ ተመለሰች?

ክፍለ ትምህርት 2

<u>መግቢያ ጥያቄዎች (ያለፈውን ክፍለ ትምህርት ከከለሱ በኋላ)</u>

1. እንግዳ ማለት ምን ማለት ነው?
2. ለቤተሰቦቻችሁ ታማኝ ናችሁ ? እስከምን ድረስ

<u>አብርሃም</u>

በጥንት ዘመን አብርሃም የሚባል ደግ ሠው ከነዓን ከምትባል ሀገር ውስጥ ይኖር ነበር። አብርሃም እጅግ በጣም ደግ እና ሠው የሚወድ አዛውንት ነበር። ምን ግዜም እንግዳ ካልመጣ በቀር ምግብ ብቻውን አይመገብም ነበር። እግዚአብሔርም ይህንን ተግባሩን ተመልክቶ አብርሃም በጣም ይወደው ነበር። ሰይጣን ግን በአብርሃም ይቀና ነበር። ስለዚህም አብርሃምን እንዴት እንደሚጎዳው ያስብ ጀመር። ከዚያም ወደ አብርሃም ቤት በሚወስደው መንገድ ላይ ተቀምጦ እንግዶችን መጠበቅ ጀመረ። ከዚያም እንግዶች ወደ አብርሃም ቤት ሲመጡ ራሱን እንደተደበደበ ሠው አቆሳስሎ ይጠብቃቸው ጀመረ። እንግዶቹም ምን ሆነህ ብለው ሲጠይቁት "አብርሃም ነው እንዲህ አርጎ የደበደበኝ እናንተም እሱ ጋር ከሆነ የምትሄዱት እንደ እኔ ደብድቦ ነው የሚልካችሁ" አላቸው። እንግዶቹም እየፈሩ ወደ አብርሃም ቤት መሄድ ተው። አብርሃም ግን ሠይጣን የሠራበትን ተንኮል ሣያውቅ እንግዶቹን መጠበቅ ቀጠለ። ለብዙ ቀናት መንገደኞቹ ወደ እሱ ቤት ሣይመጡ ሲቀር በጣም አዘነ። አንድ ቀን በመምሬ ዛፍ ስር ሶስት ሽማግሌዎች ተቀምጠው አየ። በጣም ተደስቶ ከድንኳኑ ውስጥ አገባቸው ።እንዳቸውን ተሸክሞ ሲያስገባ ሁሉም ገብተው አገኛቸው ። ደግሞም የእንዳቸውን እግር ሲያጥብ የሌሎቹንም ታጥቦ አገኘው። ሚስቱ ሳራ ለእንግዶቹ ምግብ እያዘጋጀች ነበር። በዚያ ሰዓት አብርሃምም ሆነ ሚስቱ ሣራ ልጅ ያልነበራቸው ሲሆን ሁለቱም በጣም አርጅተው ነበር። እንግዶቹም አብርሃምን የዛሬ ዓመት ልጅ ታገኛለህ አሉት። ሚስቱ ሣራ ጓዳ ሆና ሣቀች። ያላዩአት መስሏት ነበር። እነሱ ግን ሚስትህ ሣራ ስለምን ሣቀች አሉት/ እሷ አልሣቅሁም ብላ ካደች። እነሱም በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሣነው ነገር አለን ብለው ጠየቋት ከዚያም እንግዶቹ ተነስተው ሄዱ። እንደተናገሩትም በአመቱ ሣራ ልጅ ወለደች። የልጁንም ስም ይስሃቅ ብለው ጠሩት። የአብርሃም ዘርም ብዙ እየሆነ ሄደ።

<u>ይስሀቅ</u>

በጥንት ዘመን ይስሀቅ የሚባል ልጅ ነበር አባቱም አብርሃም በመባል ይታወቃል። እናቱም ሣራ ትባላለች። ይስሀቅ እጅግ ታዛዥ ልጅ ነበር ሽማግሌ አባቱንና እናቱን በመላላክ በመታዘዝ ይረዳቸው ነበር።

ከእለታት በአንድ ቀን እግዚአብሔር አምላክ የይስሀቅን አባት አብርሃምን እባክህ ልጅህ ይስሀቅን ሰዋልኝ በማለት ይጠይቀዋል። አብርሃምም ልጁ ይስሀቅ ታዛዥ እንደሆነ አውቆ በእግዚአብሔር ላይ እምነቱን አድርጎ እሺ አለ።

በጠዋት ይስሀቅን ይዞ ለእግዚአብሔር መስዋት ለማቅረብ ወደ ተራራ ይዞት ወጣ ሲሄዱም ይስሃቅ አባቱን ጥያቄ ጠየቀው።ይስሀቅ አባዬ ወዴት ነው የምንሄደው ?

አብርሃም ለእግዚአብሔር መስዋት ለማቅረብ ነው አለው። ይስሀቅ መስዋዕት ወሠውያውን ቢላዋ ይዘናል መስዋት ማቃጠያ እንጨቱንም ታዲያ በጉ የታለ ?

አብርሃምም በጉን እግዚአብሔር ያዘጋጃል አለው ይስሀቅም እሺ በማለት ጉዞአቸውን ወደ ተራራው አደረጉ።

ተራራው ላይ ወጥተው እንጨቱን አረብርበው (ደርድረው) ከጨረሱ በኋላ አብርሃም ይስሃቅን ልጄ ሆይ ለእግዚአብሔር የምሠዋው መስዋዕት በጉ አንተ ነህ አለ።

ይህን ጊዜ ይስሀቅ ታዛዥ ነበርና እሺ አንተ ካልክ በማለት ለአባቱ አንገቱን በመስጠት መሬት ላይ ተኛለት ከዚህ በኋላ ይስሀቅ ለአባቱ እንዲህ አለው አባዬ አይኔን እያየህ እንዳትራራ ገልብጠህ እረደኝ በማለት በጀርባው ተኝቶ የነበረው ይስሀቅ በሆዱ ተኛ አባቱ አብርሃምም ቢላውን አንስቶ በይስሀቅ ላይ ሊያሣርፍ ሲል እግዚአብሔር ልጅህ ይስሀቅን አትረደው የሚታረድ በግ ይሄውልህ በማለት በእጸ ሳቤቅ የታሰረ በግ ሰጠው የአብርሃምን ና የይስሃቅን ታማኝነት ተመለከተ። ስለዚህ ልጆች እናንተም ለቤተሠቦቻችሁ ታዛዥዎች ከሆናችሁ እግዚአብሔር ከመጥፎ ነገር ይጠብቃችሃል።

መልመጃ

1. አብርሃም ይኖር የነበረው በየት ሃገር ነው?
2. ሰይጣን የአብርሃምን እንግዶች ያስት የነበረው እንዴት ነው?
3. ወደ አብርሃም ቤት የመጡት ስንት ሰዎች ናቸው?
4. ሳራ የሳቀችው ለምንድን ነው?
5. የአብርሃምና ሳራ ልጅ ማን ይባላል?
6. እግዚአብሄር አብርሃምን የጠየቀው ጥያቄ ምንድን ነው?
7. ይስሃቅ አባቱን የመስዋዕቱ በግ የታለ ሲለው አብርሃም ምን ብሎ መለሰለት?
8. ይስሃቅ መስዋዕት ሊሆን ሲል የተኛው እንዴት ነው?
9. እግዚአብሄር ለአብርሃም በይስሃቅ ፋንታ ምን ዓይነት መስዋዕት ሰጠው?

ክፍለ ትምህርት 3

<u>መግቢያ ጥያቄዎች (ያለፈውን ክፍለ ትምህርት ከከለሱ በኋላ)</u>

1. በኩር ማለት ምን ማለት ነው?

ያዕቆብ

ልጆች ይገርማችኋል ይስሀቅ የሚባል አንድ ታዛዥ የነበረ ሰው እንደነበረ ተምረናል። እግዚአብሔር አምላካችንም ሁለት መንትያ ልጆች ሠጠው። አንደኛ ኤሳው ሲባል ሁለተኛ ያዕቆብ ይባላል።

ታዲያ ያዕቆብ ከወንድሙ ከኤሳው ታላቅነት ለመቀማት ብዙ ጥረት ያደርግ ነበር። ልጆች ለምን የአባቱ በረከት መሠላችሁ ታላቅ መሆን የሚፈልገው ታላቅ ከተባለ የአባቱን በረከት ይወርሳልየእግዚአብሔር ልጅ ይሆናል ስለዚህ በጣም ብዙ ግዜ ይመኝ ነበር። ከእለታት በአንድ ቀን ያዕቆብ እቤት ቁጭ ብሎ እናቱን ሲያግዝ ኤሳው ጫካ ገብቶ አድኖ የሚገድላት አውሬ አጥቶ እቤት ሲመለስ ምስር ወጥ እየሰራ ተመለከተው።

ፀሀይ ነበርና መቋቋም ስላቃተው እርቦት እባክህ ያዕቆብ ከምትሠራው ከምስር ወጥ ስጠኝ ሲለው ቡክርናህን (ታላቅነትህ) ለእኔ ስጠኝና አለው ኤሳው እርቦት ስለነበር እሺ አለ ያዕቆብም ታላቅ መሆንን አገኘ።

ታዲያ ይስሀቅ አባታቸው እያረጀ ሄደ ስለዚህም በረከት ለታላቅ ልጅ ነበርና የሚያስተላልፈው ኤሳውን አስጠርቶ አደን ሄደህ ምግብ ሠርተህ አምጣልኝ ልባርክህ ነው በማለት ያዘዋል ኤሳው ወደ አደን ሲሄድ ያዕቆብ በግ አርዶ ምግብ አዘጋጅቶ ወደ አባቱ እልፍኝ የበጉን ቆዳ ለብሶ ይገባል። አባቱ ይስሃቅ በእርጅና ምክንያት አይኑ ደክሞ ነበርና አባቱ ያዘዝከኝን አመጣሁ በማለት ምግቡን አቀረበለት አባቱም አንተ ማን ነህ በማለት ጠየቀው እርሱም እኔ ኤሳው ነኝ በማለት መለሠለት ምነው ድምፅህ የያዕቆብ መሠለኝ ና ሠውነትህ ልዳበሰው ሲለው ጠጋ አለ ዳበሠው የበጉ ፀጉር ስለለበሰ ኤሳውን መሠለው ሠውነትህ የኤሳውን ይመስላል። አለው። ኤሳው ሠውነቱ ፀጉር ነበርና ምግቡን በልቶ ያዕቆብን ባረከው።

ኤሳውም ያደነውን አርዶ ምግብ ሠርቶ አመጣ ነገር ግን ይስሀቅ ሁሉንም በረከት ለያዕቆብ ሠጥቶት ነበር። አንተ ማንህ አለው። ኤሳው ነኝ አለ አሁን የመጣው ማነው ? ያዕቆብ ይሆናል እርሱን ባረከት ሌላ የቀረ በረከት አለ ብሎ ጠየቀ ? የለም ወንድም ይዣልህ ብዬ መርቄዋለሁ ሁሉን ለሡ ሠጥቸዋለው አለው።

መልመጃ

1. ሁለቱ የይስሃቅ ልጆች ማን ይባላሉ?
2. ያዕቆብ የኤሳውን ብኩርና የፈለገው ለምንድነው?
3. ያዕቆብ የኤሳውን ብኩርና ያገኘው እንዴት ነው?

ክፍለ ትምህርት 4

<u>መግቢያ ጥያቄዎች (ያለፈውን ክፍለ ትምህርት ከከለሱ በኋላ)</u>

1. ህልም ማለት ምን ማለት ነው ?

ቅዱስ ዮሴፍ

ያዕቆብ የተባለ ሠው የወለዳቸው 12 ልጆች ነበሩት ። ከ12 አንዱ ዮሴፍ የሚባለው ሲሆን እግዚአብሔርን ስለሚፈራ አባቱ ያዕቆብም ስለሚወደው ወንድሞቹ ይጠሉት ነበር።

ከእለታት በአንድ ቀን ህልም አየ። በህልሙም ከወንድሞቹ ጋር ሆነው ስንዴ ሲያጭዱ እነሱ የያዙት የስንዴ ነዶ ለሱ ሊሠግድ እያለ ሲነግራቸው እሱ እኛን ሊገዛ በማለት በወንድማቸው ላይ ሁሉም ተንኮል አሰቡ።

በሁለተኛው ቀን ህልም አለመ መጥቶ ነገራቸው ህልሙ ጨረቃዎች ከበው ለጸሀይ ሲሠግዱ ነበር። ይህ ልጅ ሳይገዛን ቶሎ ብለን እንግደለው እያሉ ሲማከሩ አባቱ ያዕቆብ ለወንድሞቹ ምግብ እንዲያደርስ ላከው። እርሱም ለወንድሞቹ ምግቡን ይዞ እረኝነት የሚጠብቁትን ቦታ ቢሄድ አጣቸው። ለካ እነሱ ተደብቀው ነበር።

እርሱም ፈልጎ ሲያገኛቸው የለበሰው አዲስ ልብስ ነበር በእርሱም ተናደው ስለነበር ከጉድጓድ ከተውት ይመካከሩ ጀመር እዚሁ እንግደለው እየተባባሉ ቆይተው። እስማኤላውያን ነጋዴዎች ሲመለከቱ ከጉድጓድ አውጥተው ልብሱን ገፈው ለነጋዴዎች በ20 ብር ሸጡት።

ከዚህ በኋላ በግ አርደው የዮሴፍ ልብስ በደም ነክረው ለያዕቆብ ሠጡት ያዕቆብም እጅግ አለቀሠ መፅናናት ግን አልፈለገም።

ዮሴፍን ወስደው ጲጢፋራ ለሚባል የግብፅ ንጉስ የዘበኛ አለቃ ሸጡት። እርሱም ዮሴፍን አመነው ነገር ግን ሚስቱ ከሳው በውሸት ዮሴፍ እስር ቤት ተጣለ እዛ እያለ የንጉሱ ሁለት አገልጋዮች ጥፋት በማጥፋት ከዚያ ተጣሉ።

ሁለቱ አገልጋዩች ህልም አለሙ። በጠዋትም አዝነው የሚተረጉምልን አጣን አሉት። እርሱም ህልማቸውን ፈታላቸው ህልሙም የእንጀራ አበዛዎቹ አለቃን ህልሙ ሲፈታለት በሶስት ቀን ውስጥ በእንጨት ላይ እንደሚሰቀል የጠጅ አሳላፊዎች አለቃ ደግሞ ወደ ስራው እንደሚመለስ ነገራቸው ። ህልሙም እንደተረጎመላቸው ሆነ።

ከጊዜ በኋላ ንጉሱ ፈርኦን ህልም አለመ የሚተረጉምለት አጣ ። የጠጅ አሳላፊዎቹ አለቃ በኋላ ላይ ዮሴፍን አስታወሰው ። ዮሴፍ ተጠራ የፈርኦንን ህልም ፈታለት ስለሚኖረው የ ጥጋብና የ ረሃብ አመታት በህልሙ አማካኝነት ተነገረ። ዮሴፍም በግብጽ ሁሉ ላይ ተሾመ። የጥጋቡ ዘመን ላይ ብዙ እህል ተሰበሰበ ሌላው የረሃብ ዘመንም መጣ በሌላም ምድር ረሃብ ስለ ነበር የዮሴፍ ወንድሞች እህል እንዲያመጡ ያዕቆብ ወደ ግብጽ ላከችው።

ዮሴፍም ወንድሞቹን አወቃቸው ። እነርሱ ግን አላወቁትም ነበር በኋላም በተለያዩ መንገዶች ወንድሞቹን ፈተናቸው በኋላም ያዕቆብ ወደ ግብጽ ሄደ ቤተሰቡም ሁሉ በግብጽ መኖር ጀመሩ ።

መ ልመጃ

1. ዮሴፍ ስንት ወንድሞች ነበሩት?
2. ዮሴፍን ወንድሞቹ ለምን ሸጡት?
3. ዮሴፍን በንጉሱ እንዲሾም ያደረገው ምንድን ነው ?

ክፍለ ትምህርት 5

<u>መግቢያ ጥያቄዎች (ያለፈውን ክፍለ ትምህርት ከከለሱ በኋላ)</u>

1. ተማሪዎች አንድ ህጻን ልጅ በቅርጫት ተደርጎ ውሃ ላይ ቢጣል ምን የሚሆን ይመስላቹሃል?

ሊቀ ነቢያት ሙሴ

እስራኤላውያን ግብጽ ውስጥ በግዞት ተይዘው የሚንገላቱበት ወቅት ነበር። በዘመኑ የነበረው ንጉስ የተወለደው ወንድ ህጻን በጠቅላላው እንዲገደል አዟል ከእስራኤላውያን ወገን የሆነች ስሟ ኢዮካበድ የተባለች ሴት ጸንሳ ነበርና ወለደች። የተወለደው ወንድ ነበረና አይኗ እያየ እንዳይገድሉት ፈርታ በቅርጫት አድርጋ የንጉሱ ልጅ ገላዋን ትታጠብበት ከነበረበት ባህር ላይ ሰደደችው።

የንጉሱም ልጅ በቅርጫት በተመለከተችው ጊዜ ፊቱ የሚያምር ህጻን በውስጡ አገኘች። ለአገልጋዮቿ በቅርብ ወልዳ ልጅ የተገደለባት ሴት እንዲፈልጉ በማድረግ ዮካብድ ጡት እያጠባች እንድታሳድገው አመጣት። ከባህር የተገኘ ነው ስትል ሙሴ ብላ ስሙን ጠራችው። እያደገ ሲሄድም ወደ ንጉሱ ወሰዱት

ንጉሱ ግን ንግስናውን የሚቀማው ስለመሰለው ማደግ የለበትም አላት ። የ ንጉሱ ልጅም ለመነችው። ንጉሱም እሳትና ፍርፍር በፊቱ አስቀምጣለው አንስቶ የሚበላው ፍርፍር ከሆነ እገድለዋለው አላት በዚህም ተስማሙ። በሙሴም ፊት የእሳት ፍምና ምግብ ተቀመጠ ሙሴም እጁን ወደ ምግቡ ሲሰድ የእግዚአብሔር መልዓክ እጁን ወደ ፍሙ በማድረግ አንስቶ ከአፉ ከተተው ከዚህ ጊዜ ጀምሮ አፉ ኮልታፋ ሆነ ። ሙሴም እያደገ ሲሄድ በንጉሱ እየተወደደ መጣ ። ከእለታት በአንድ ቀን አንድ ግብጻዊ እስራኤላዊውን ሲያንገላታው ተመልክቶ ገደለው። ከግብጽም ተባሮ በስደት ሄደ በስደት በሄደበት ቦታ ኢትዮጵያዊቷን የዮቶር ልጅ አግብቶ ሲኖር በሲና ተራራ ብርሃን ተመልክቶ ወደተራራው በወጣ ጊዜ እግዚአብሔርም የቆምክበት ስፍራ የተቀደሰ ነውና ጫማህን ከእግርህ አውጣ አለው። ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር በሲና ተነጋገረ ህዝበ እስራኤልን ከግብጽ ምድር የምታወጣቸው አንተ ነህ በማለት ነገረው። ሙሴም እኔ ኮልታፋ ነኝ በምንስ እናገራለው አለ ። ወንድምህ አሮን አንደበት ይሆንሃል ብሎ ወደ ግብጽ ላከው። ሙሴ ወደ ግብጽ ሄዶ በፈርኦን ፊት ቆሞ እግዚአብሔር ህዝቤን ልቀቅ ብሎሃል አለው ፈርኦንም ልቡ ደነደነ ። ሙሴም የያዘውን በትር በፈርኦን ፊት እባብ አደረገው። ፈርኦንም ይህንንማ የእኔም አስማተኞች ያደርጉት የለምን በማለት አስማተኞችን ጠርቶ ዱላቸውን ወደ እባብነት ለወጡ የሙሴ እባብ ግን የአስማተኞቹን እባብ ዋጠቻቸው ። ሙሴም ፈርኦንን አስር ቅጣት ከእግዚአብሔር እያስላከ አስቀጣው ፈርኦንም በአስረኛው ሞተ በኩር ህዝቡን ለቀቀ። ህዝቡም ከግብጽ ምድር ወጡ። ብዙ ከሄዱ በኋላ ግን አንድ ችግር ገጠማቸው ከፊታቸው የቀይ ባህር ከኋላቸው ለቅቄያለው ያለው የፈርኦን ሰራዊት ተከበቡ ህዝቡም በጠቅላላው በሙሴ ላይ አጉረመረሙ። ሙሴም ባህሩን በዱላው በመታው ጊዜ እንደግርግዳ ቀጥ አለ ለሁለት ተከፈለ በመሃል ተሻገሩ የፈርኦን ሰራዊትና ፈርኦን በባህሩ መካከል ለመሄድ ሲገቡ ባህሩን ሙሴ ዘጋው ፈርኦንና ሰራዊቱ በባህር ውስጥ ሰጠሙ። ህዝበ እስራኤልም የሙሴ እህት ማርያም ከበሮ አንስታ በዝማሬ እግዚአብሔርን አመሰገኑ።

መልመጃ

1. *ሙሴ ማለት ምን ማለት ነው?*
2. *ሙሴ ህጻን እያለ ንጉሱ ምን አደረገው ?*
3. ባህሩን ሙሴ እንዴት ነው የከፈለው ?

ክፍለ ትምህርት 6

መግቢያ ጥያቄዎች (ያለፈውን ክፍለ ትምህርት ከከለሱ በኋላ)

1. ወንጭፍ ማለት ምን ማለት ነው?

ነቢዩ ሳሙኤል

ከብዙ አመት በፊት አንዲት ሃና የምትባል ልጅ ስላልነበራት ከቤተመቅደስ በር ላይ ተደፍታ እጅግ ታለቅሳለች። በዚያን ጊዜ በቤተመቅደስ ውስጥ ካህኑ ኤሊ የሚባል ነበር። እርሷ ግን ከእግዚአብሔር ጋር በፀሎት ስትነጋገር ከአጠገቧ ያለውን ሰው እንኳን አትሰማም ነበር። እግዚአብሔር ሆይ ልጅ የማትሠጠኝ እስከመቼ ነው። እያለች ስታለቅስ ያያት ካህኑ ኤሊ ከሁኔታዋ የሰከረች መሰለችውና አንቺ ሴት እስከመቼ ስካርሽ አይለቅሽም በማለት ተናገራት እርሷግን አንተ የእግዚአብሔር ካህን እኔ ወይን ጠጥቼ የሰከርኩ አይምሰልህ ልጅ እንዲሠጠኝ እግዚያብሔርን እየለመንኩት እንጂ አለችው።

ካህኑ ኤሊ ይህን በሠማ ግዜ ባረከትና እግዚአብሔር ፀሎትሽን ይስማሽ አላት እርሷም ተነስታ ወደቤቷ ሄደች። ከብዙ ጊዜ በኋላም ሃና ፀነሳ ወንድ ልጅ ወለደች ስሙንም ሳሙኤል ብላ ጠራችው።

እድሜውም ትንሽ ከፍ ሲል እግዚአብሔር የሰጠኝ ልጅ ስለሆነ በእግዚአብሔር ቤት ይኑር ብላ ለካህኑ ዔሊ እየታዘዘ ማደግ ጀመረ ።ሳሙኤል ፀሎት የሚወድ ካህኑን ዔሊን የሚላላክ ነበር ካህኑ ዔሊ ሁለት ልጆች ነበሩ የአንደኛው ስም አፍኒን የሁለተኛው ስም ደግሞ ፊንሃስ ይባሉ ነበር።

አባታችን ለዔሊ የማይታዘዙ እግዚአብሔርን የማያከብሩ ነበሩ። አባታቸው ኤሊም አጠበቆ ተቆጥቷቸው አያውቅም ነበር። በቤተመቅደስ ተኝተው ሳሙኤል ሳሙኤል የሚል ድምፅ መጣ ሳሙኤልም ካህኑ የጠራው መስሎት አባቴ ጠራሃኝ አለ አልጠራሁህም አለው። ሁለተኛ ሳሙኤል ሳሙኤል አለው። እርሱም ወደ ካህኑ ኤሊ ሄዶ ጠራሃኝ አለው ካህኑም እግዚአብሔር መሆኑን ሲረዳ ተናገር እሰማለሁ በለው አለው። ሳሙኤልም እርሱ እንዳለው አደረገ ተባረከ። አፍኒንና ፊናስን ግን ቀሠፋቸው።

ንጉስ ዳዊት

ከብዙ ሺህ ዓመት በፊት በእስራኤል አገር ቤተልሔም በተባለች ከተማ ከይሁዳ ነገድ ለሆነ እሴይ ለሚባል ሰው ስምንት ወንድ ልጆች ነበሩት። የስምንተኛ ልጁ ስም ዳዊት ይባል ነበር።

በዚያን ዘመን ሳኦል የተባለው የእስራኤል ንጉሥ ለእግዚአብሔር ለነቢዩ ሳሙኤል "በቀንድ ዘይት ሞልተህ ወደ ቤተልሔም ሂድ ከናቅሁት ከሳኦል በኋላ በእስራኤል ላይ ንጉሥ የሚሆን ከቤተልሔማዊው ከእሴይ ልጆች መካከል አዘጋጅቻለሁ" አለው።

ሳሙኤልም እግዚአብሔር የተናገረውን አደረገ እሴይም ሰባቱን ልጆቹን በነቢዩ ፊት አሳለፋቸው ሳሙኤልም "እግዚአብሔር እነዚህን አልመረጠም የቀረ ልጅ አለህን ? አለው።

እርሱም "ታናሹ ገና ቀርቶአል እነሆም በጎችን ይጠብቃል" አለ። ሳሙኤል" እርሱ እስኪመጣ ድረስ አንቀመጥምና ልከህ አስጠራው አለው።

እሴይም ልኮ ዳዊትን አስጠራው ዳዊት ግን እግዚአብሔርን በበገና እያመሠገነ በጎች እየጠበቀ ነበር። መልዕክተኞችም አባት እሴይ ይፈልግሃልና ቶሎ ና ተብልሃል ብለው ለዳዊት ነገሩ እርሱም የ 12 ዓመት ብላቴና ነበር። በፍጥነትም ወደ አባቱ መጣ ሲመጣም እግዚአብሔር እንደልቤ የሆነው ዳዊት እርሱ ነው የንግስናውን ዘይት ቀባው አለው ሳሙኤል ተነስቶ ዳዊት የንግስና ዘይቱን ቀባው የእግዚአብሔር መንፈስ በዳዊት ላይ አደረ።

ከእለታት በአንዱ ቀን ፍልስጤማውያን እስራኤላውያን ጦርነት ሊገጥሙ በጦር ሜዳ ተገናኘ ፍልስጤማውያን ጎልያድ የሚባል እጅግ አሰፈሪ ቁመቱ ረጅምና ወፍራም ወታደር ነበራቸው። ጎልያድ ማነው ከእናንተ እኔን የሚገጥመኝ የእግዚአብሔር ህዝብ ነን የምትሉት እስኪ ከእኔ ጋር የሚጋጠም ወታደር ላኩ እያለ ሲፎክር የ 12 ዓመቱ ዳዊት ወደ ጦርነቱ ሜዳ ለወንድሞቹ ምግብ ለማድረስ መጣ። ዳዊትም ጎልያድ በእስራኤላውያን ላይ ሲፎክር ሰማው። ለሳኦልም እኔ ከጎልያድ ጋር እዋጋለው ብሎ ተናገረ። እነርሱ ግን አንተ ልጅ ነህ እርሱ ትልቅ ጦረኛ ነው አትችለውም አሉት።እግዚአብሔርም እንደሚረዳው ዳዊት ተናገረ።የጦር ልብስ አለበሱት ና ላኩት ነገርግን ስለከበደው አወለቁለት። በትሩን በእጁ ይዞ ወንጭፍ አዘጋጅቶ አምስት ጠጠሮችን ለቅሞ ከጎልያድ ጋር ሊጋጠም ገባ ህዝቡ ሁሉ ፀጥ አለ ጎልያድ ተናድዶ ይሄንን ልጅ ነው ከእኔ ጋር ለመጋጠም የምትልኩት ስጋህን ቆራርጬ ለአሞራ እሰጣለሁ ብሎ ጎልያድ ፎከረ ዳዊት ግን አንተ በተገዳደርከው በእግዚአብሔር ስም እመጣብሃለው። ብሎ አንድ ድንጋይ በማንሳት ወንጭፍ ውስጥ ከተተና ወነጨፈው ድንጋዩ ከጎልያድ ግንባር ውስጥ ገብታ ተቀረቀረች ረጅሙና ወፍራሙ ጎልያድ ሰው በፊቱ ተደፋ ዳዊት እሮጦ ሄዶ የጎልያድን ሰይፍ በማንሳት አንገቱን ቆረጠው ፍልስጤማውያን ሮጠው ሲሸሹ እስራኤላውያን ዳዊትን ይዘው እግዚአብሔርን አመሠገኑ።

መልመጃ

1. ሃናን የባረካት ካህን ስሙ ማን ነበር?
2. ሁለቱ የኤሊ ልጆች ስማቸው ማን ነበር?
3. ሳሙኤል እግዚአብሔር ሲጠራው ምን ብሎ መለሰለት?
4. ዳዊት አባቱን የሚያገለግለው በምንድን ነው ?
5. እግዚአብሔርን የሰደበው ፍልስጤማዊ ማን ይባላል?
6. ዳዊት ጎልያድን የገደለው በምንድን ነው ?

ክፍለ ትምህርት 7

<u>መግቢያ ጥያቄዎች (ያለፈውን ክፍለ ትምህርት ከከለሱ በኋላ)</u>

1. ካህን ማለት ምን ማለት ነው?

<u>ካህኑ ዘካርያስ</u>

በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ የሚያገለግል ዘካርያስ የሚባል ካህን ነበር። ሚስቱም ኤልሣቤጥ ትባላለች። ሁለቱ የእግዚአብሔር ሠዎች ነበሩ። እግዚአብሔርን በማክበርና በመፍራት ይኖሩ ነበር ነገር ግን ልጅ አልነበራቸውም። ሁል ጊዜ ፀሎታቸው እግዚአብሔር ልጅ እንዲሠጣቸው ነበር። ከእለታት በአንድ ቀን ካህኑ ዘካሪያስ በቤተ መቅደስ ውስጥ በክህነት አገልግሎት እጣን በማጠን ላይ ሳለ የእግዚአብሔር መልአክ ተገለጠለት። ዘካርያስም ደነገጠ መልአኩም ዘካሪያስ ሆይ አትፍራ ጸሎትህ ተሠምቶልሃል ሚስትህ ኤልሳቤጥ ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች ስሙም ዮሐንስ ይባላል አለው።

ዘካሪያስ ግን እኔ አርጅቻለሁ እያለ ከእግዚአብሔር መልዐክ ጋር ተከራከረ የእግዚአብሔር መልዐክም የነገርኩህን አላመንክምና እሱ እስኪወለድ አንተ ዲዳ ትሆናለህ ብሎት ወደ ሰማይ አረገ። ሕዝቡ ስለቆየ ተጨነቁ ከቤተ መቅደስም ሲወጣ መናገር አይችልም ነበር። የሆነውን ቢጠይቁትም መናገር አልቻለም በእጅም እያመለከታቸው ኖረ። ሚስቱ አልሳቤጥ ፀነሠች ከዘጠኝ ወር በኋላ ተወለደ ስሙ ሊያወጡ ሲፈልጉም ዘካርያስን መጥተው ጠየቁት እርሱም በመፃፍ ሊያሣያቸው ሲል አፉ ተከፈተ አጣርቶ መናገር ቻለ ስሙን ዮሐንስ ብሎ ጠራው። የህጻኑ ነገር በሃገሩ ሁሉ ተወራ።

መልመጃ

1. የዘካሪያስ ሚስት ስሟ ማን ይባላል?
2. ዘካሪያስ ዲዳ የሆነው ለምንድን ነው?
3. የዘካሪያስ እና ኤልሳቤጥ ልጅ ስሙ ማን ይባላል?

<u>ሐዲስ ኪዳን</u>

<u>ቅዱስ በርተሎሜዎስ</u>

ቅዱስ በርተሎሜዎስ አልዋህ ወደሚባል ሀገር ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር መጓዝ ጀመሩ። ነገር ግን መንገዱን አያውቁትም ነበርና በጥየቃ ነበር የሚጓዙት። ከዚያም አንድ ሚራራ ነጋዴ አገኙና እንዲያደርሣቸው ጠየቁት። እርሱ ግን እይሆንም አላቸውና ሄደ።

በዚህ ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስ እና ሐዋርያው በርተሎሜዎስ ተመካከሩ። ሌላ ነጋዴ ሲመጣም ቅዱስ ጴጥሮስ ይህን ባሪያዬን በሀገረ አልዋህ ልሸጠው ፈልጌአለሁ። እባክህ ወደ ሃገርህ ውሰደኝ ሲል ጠየቀው። ያም ነጋዴ ለብዙ ጊዜ ከሀገሬ ወጥቼ የምኖር በመሆኔ ለቤቴ አገልጋይ የሚሆን ሠው አጥቼ እኖር ነበር። ዛሬ አገኘሁ። ለመሆኑ ሙያው ምንድን ነው? ብሎ ጠየቃቸው ቅዱስ ጴጥሮስም "ወይን ጠባቂ ነው" አለው። ያ ነጋዴ እጅግ በጣም ብዙ ወይን ስለነበረው በ 30 እስታቴር በርተሎሜዎስን ከቅዱስ ጴጥሮስ ገዛው። ቅዱስ ጴጥሮስም ገንዘቡን ከነጋዴው ከተቀበለ በኋላ አደራ ለሌላ ጌታ እንዳትሸጠው፣ መከራም እንዳታበዛበት ሲል ነጋዴውን ለመነው። ባለ ፀጋው የግመሎቹን ሸክም ሲያስተካክል ቅዱስ ጴጥሮስ ገንዘቡን ደብቆ ለበርተሎሜዎስ በመስጠት "ለድሾች መፅውተው" አለውና ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ።

ነጋዴውና በርተሎሜዎስ በበረሃው ውስጥ መንገዳቸውን ቀጠሉ። አልዋህ እንደደረሱም ነጋዴው በርተሎሜዎስን የወይን ጠባቂዎች አለቃ አድርጎ ሾመው። ወይን እየጠበቀ እየከተከተ ና እየተከለ ለ 40 ቀናት ያህል በሥራ ተጠምዶ ተቀመጠ። "ጌታዬ ሆን ወንጌልህን ሳልሰብክ፣ ትዕዛዝህን ሳልፈፅም ተቀምጪ መቅረቴ ነውን" እያለ ያለቅስ ነበር።

አንድ ቀን ባለፀጋው የወይኑን ቦታ ሊያይ ሲመጣ እባብ ከጉድጓድ ወጥቶ ነክሦውና መርዙ ኃይለኛ ነበርና በሠውነት ውስጥ ተሠራጭቶ ለሞት አበቃው። ወዳጅ ዘመዶቹም ለለቅሶ ተሠበሠቡ። በርተሎሜዎስ ግን ወደ እግዚአብሄር ይፀልይ ነበር። የቤቱም ሠዎች "አንተ ጨካኝ አሸከር ጌታህ ሲሞት እንደማልቀስ አፍጥጠህ ታየናለህ" እያሉ ጮኹበት።

በርተሎሜዎስ ግን ጸሎቱን እስኪፈፅም ታገሣቸውና ያንን ባለፀጋ በስመ እግዚአብሔር ከሞቱ አስነሣው። ያም ባለፀጋ ከእንቅልፉ እንደሚነቃ አፈፍ ብሎ ተነስቶ ለዚህ ያበቃው በርተሎሜዎስ መሆኑን መሠከረ። በዚህም የተነሣ ባለፀጋውና የተሠበሠበው ህዝብ ሁሉ በተደረገው ተዓምር ተገረው። በበርተሎሜዎስ ስብከትም አምነው ተጠመቁ።

መልመጃ

1. ቅዱስ በርተሎሜዎስ ወደ የት ሃገር ነው የሄደው?
2. የቅዱስ በርተሎሜዎስ አሰሪ ቅዱስ በርተሎሜዎስን በስንት ብር ነው የገዛው?
3. አሰሪው ምን ሆኖ ነው የሞተው ?
4. ቅዱስ በርተሎሜዎስ አሰሪውን ከሞት ያስነሳው እንዴት ነው?

ክፍለ ትምህርት 8

<u>መግቢያ ጥያቄዎች (ያለፈውን ክፍለ ትምህርት ከከለሱ በኋላ)</u>

1. አሳ ማስገር ማለት ምን ማለት ነው።

<u>ቅዱስ ያዕቆብ</u>

ቅዱስ ያዕቆብ የቅዱስ ዮሐንስ ወንድም ነበር። ሥራውም አሣ ማጥመድ ነበር። ጌታችንም በዚህ ላይ እንዳሉ አሱን ከወንድሞቹ ጋር ለአገልጋይነት መረጣቸው።

ቅዱስ ያዕቆብ በሚያስተምርበት ወቅት በአንድ ከተማ ውስጥ የሚኖሩ ሁለት ጠንቋዮች ነበሩ። ስማቸውም ፊልጦስ እና ሄሮሞጌኒስ ነበር። ከእነዚህ ሁለት ጠንቋዮች አንደኛው ፊሊጦስ በቅዱስ ያዕቆብ ስብከት ማመኑን ለጓደኛው ሄሮሞጌኒስ ነገረው። ሄሮሞጌኒስም ጓደኛው ጥንቆላውን በመተው ተበሳጨ። ከዚህም ፊሊጦስን በአስማት አሣሠረው። ፊሊጦስም መጥቶ እንዲያድነው ለቅዱስ ያዕቆብ መልዕክት ላከበት።

ሄሮሞጌኒስ ጓደኛውን ፊሊጦስን እንዳሠረው ሁሉ ቅዱስ ያዕቆብን ለማሠር ፈለገ። ከዚያም አጋንንትን ቅዱስ ያዕቆብን አሥረው እንዲያመጡት ላካቸው። የተላኩት አጋንንት ግን ቅዱስ ያዕቆብን ሳይሆን አጋንንቱን ሄሮሞጌኒስን ጠፍረው አመጡት። ያን ጊዜ ቅዱስ ያዕቆብ ፊሊጦስን ፈታው።

ፊሊጦስ በተራው ክርስቲያን ስለሆነ ጓደኛው ሄሮሞጌኒስ እንዲፈታ ቅዱስ ያዕቆብን ለመነው። ቅዱስ ያዕቆብም እኛ ክፉን በክፉ ስለማንቃወም በሠይጣን እየተሠቃየህ እንዳትኖር ከክርስቶስ ምህረትን ለምነንልሃል" በማለት ከታሠረበት እንዲፈታ አደረጉ።

አስማተኛው ሄሮሞጌኒስም በክርስቲያኖች ሃይል እና ደግነት ተማርኮ ክርስቲያን ሆነ። የጥንቆላ መፃህፍቱን እና እቃዎቹን ሁሉ አምጥቶ በቅዱስ ያዕቆብ እግር ስር አቃጠላቸው።

መልመጃ

1. ቅዱስ ያዕቆብ የማን ወንድም ነው?
2. ሄሮምጌኒስ በጓደኛው የተበሳጨው ለምንድን ነው?
3. ቅዱስ ያዕቆብን አስረው እንዲያመጡ የተላኩት እነማን ናቸው?
4. ሄሮምጌኒስ ክርስቲያን ከሆነ በኋላ ምን አደረገ።

ቅዱስ ጴጥሮስ

ጴጥሮስ የተወለደው በገሊላ ባህር አጠገብ በምትገኘው በቤተ ሣይዳ ነው። ትልቅ ሲሆንም ከወንድሙ ከእንድርያስ ጋር ከገሊላ ባህር ላይ አሣ ያጠምድ ነበር። አንድ ቀን ወንድሙ እንድርያስ ከጌታችን ጋር አስተዋወቀው። እሱም ከዚያን እለት ጀምሮ ጌታን ተከተለው።

አንድ ቀን ጌታችን ስለ ሞቱ በሚነግራቸው ጊዜ ጴጥሮስ እንደማይከዳው ለጌታ ማለለት። ጌታችን ግን ዶሮ ሳይጮህ ሶስት ጊዜ ትክደኛለህ አለው።

ከዚያም ጊዜው ሲደርስ ኢየሱስ በአይሁድ እጅ ተይዞ። ሐዋርያቱም ተበተኑ። ጴጥሮስም ጌታችን ተይዞ በሚሄድበት ሰዓት በሩቅ ተደብቆ ይከተለው ነበር። ወደ ቀያፋ ጊቢ ገብቶ በተቀመጠበት ሠዓትም እንዲት አገልጋይ ወደ እርሱ ቀርባ አንተ ደግሞ ከገሊላው ኢየሱስ ጋር ነበርክ አላቸው። እርሱ ግን የምትይውን ሠው አላውቀውም ብሎ ካደ። ወደ በሩም ሲወጣ ሌላኛዋ ሴት አየችውና ይህ ሠው ከናዝሬቱ ኢየሱስ ጋር ነበር አለች። እርሱ ግን ደግሞ አላውቀውም ብሎ ደግሞ ካደ። ጥቂት ቆይቶም በዚያ አካባቢ እሣት ይሞቁ የነበሩ ሠዎች ጴጥሮስን አይተውት አነጋገርህ ያስታውቃል አንተ የኢየሱስ ወገን ነህ አሉት። እሱ ግን አላውቀውም ብሎ ከሶስተኛ ጊዜ ካደ። ወዲያውም ዶሮ ጮኸ። ጴጥሮስም ዶሮ ሳይጮህ ሶስት ጊዜ ትክደኛለህ ያለው ኢየሱስ ቃል ትዝ አለው። ወደ ውጭ ወጥቶ መራራ ለቅሶ አለቀሰ። ከዚህ ጊዜ በኋላ የክርስቶስ ታማኝ ተከታይ ሆኖ ኖረ ።

መልመጃ

1. የቅዱስ ጴጥሮስ ስራ ምን ነበር?
2. ጴጥሮስ ስንት ጊዜ ካደ?
3. ጴጥሮስ ሶስት ጊዜ መካዱን ያስታወሰው ምን ሲሆን ነው?
4. ጴጥሮስ የጌታ ንግግር ትዝ ባለው ጊዜ ምን አደረገ?

ክፍለ ትምህርት 9

<u>መግቢያ ጥያቄዎች (ያለፈውን ክፍለ ትምህርት ከከለሱ በኋላ)</u>

1. ሽፍታ ማለት ምን ማለት ነው ።

ቅዱስ ዮሐንስ

አንድ ጊዜ ቅዱስ ዮሀንስ ከኤፌሶን ከተማ ተነሥቶ ክርስቲያኖችን ለማስተማር ሲዘዋወር ወደ አንድ ትልቅ ከተማ ገባ። በዚያች ከተማ አባትና እናቱ የሞቱበት ነገር ግን በጠባይ በእምነቱ እና በቅልጥፍናው ክርስትያኖች ሁሉ የሚወዱት ጊልስ የሚባል ልጅ ነበር። እንደመጣም ጊልስን ወሰደው እንዲያስተምረው ለቅዱስ ዮሐንስ ሰጡት።

ቅዱስ ዮሐንስም ጊልስን ወደ ከተማዋ ጳጳስ ወስዶ በአደራ ሰጣቸው እሳቸውም ተንከባክበው አኖሩት በኃላም ተጠመቀ።ከጥቂት ጊዜ በኃላ ግን እኒያ ጳጳስ ስራ ስለበዛባቸው ጊልስን እንደ በፊቱ መከታተል ተወ። እርሱም ቀስ በቀስ ጠጪ፣ ቁማርተኛና ተደባዳቢ ከሆኑ ወጣቶች ጋር መዋል ጀመረ።

አንድ ቀን ማታ በአንድ ቤት ከጓደኞቹ ጋር ሲጠጡ አመሹ ሁሉም ሰክረው ሲወድቁ እሱ ብቻ ቀረ። የሁሉንም መጠጥ ሂሳብ ከፍሎ ገንዘቡን ጨረሰ። በሚቀጥለው ቀን ለጓደኞቹ ለናንተ ስል ገንዘቤን ጨረሼለሁ አሁን ኪሴ ባዶ ነው ሲል ነገራቸው ጓደኞቹም እኛ ከየት የምና መጣ መስለህ ? ባገኘህው አጋጣሚ ስረቅ ብለው መከሩት ከዚያም የሰው ቤት ሰብሮ ዘረፈ። አንድ ቀን ሰው ሲደበድብ ነፍሱ በእጁ ስለጠፋች ጊልስና ጓደኞቹ ከተማውን ለቀው ጠፉ።

ከጥቂት ጊዜ በኃላ የጊልስ ስም በአካባቢው ነገሰ የወንበዴዎች አለቃ በመሆኑ ሰው ሁሉ ይፈራው ጀመር። ከጥቂት አመታት በኃላ ወንጌላዊ ዮሐንስ ወደዚያች ከተማ ተመልሶ መጣ። እኒያን ጳጳስ ስለ ወጣቱ ጊልስ ጠየቃቸው። እሳቸውም ጊልስ ዋንኛ ወንበዴ መሆኑን እያዘኑ ገለፁለት ዮሐንስ ይህንን ሲሰማ አዘነ። ወዲያው ያለበት ጠይቆ በፈረስ እያጋለበ ሄደ። በተባለው ስፍራ ሲደርስ ሁለት ሽፍቶች አገኙት ጩቤያቸውን መዘው ከፊቱ ቆሙ ቅዱስ ዮሐንስም ከመግደላችሁ በፊት እባካችሁ ወደ አለቃችሁ ውሰዱኝ ለእኔ እርሱ የድሮ ጓደኛዬ ነው አላቸው። እነሱም ወደ አለቃቸው ወስዱት ጊልስም ዮሐንስን ሲያየው ደንግጦ መሮጥ ጀመረ ቅዱስ ዮሐንስ ልጄ ለምን ትሸሸኛለህ እኔ አባትህ ምንም የሚጎዳ መሳሪያ አልያዝሁም አለው። ያጨካኝ ሽፍታ ጊልስም አለቀሰ ። ጓደኞቹንም ደህና ሁኑ እኔ ወደ ጌታዬ መመለሴ ነው ብሎ መሣሪያውን ጥሎ ከቅዱስ ዮሐንስ ጋር ተመለሰ። ቤተክርስቲያንም እድሜ ልኩን ሲያገለግል ኖረ። ይህ ሐዋርያ ጌታችንን እስከ መስቀል ድረስ ያልተለየውና እመቤታችንንም በአደራ ከጌታችን የተቀበለ ነው ።

ሐዋርያው እንድርያስ

ይህ ሃዋርያ የጌታ ሃዋርያ ከመሆኑ በፊት የመጥምቁ ቅዱስ ዮሀንስ ደቀ መዝሙር ነበር። ዮሀንስ መጥምቁ የሚ ለውን እየሰማ ይህስ እውንተኛ የእግዚአብሄር ነቢይ ነው ንጉሱን በንግስናው የማይፈራ እያለ ደቀ መዝሙር ሆኖ ሲኖር ጌታችን መጥቶ በሐዋርያነት መረጠው ። ከአስራ አንዱ ሀዋርያት ቀድሞ የተመረጠው እርሱ ነው። በባህር አጠገብ አሳ በማጥመድ ላይ ሳለ ከወንድሙ ከኬፋ ጋር ተጠራ። ወንድሙ ኬፋን ለሐዋርያነት ሲመርጠው ኢየሱስ ክርስቶስ ከእንግዲህ ጴጥሮስ ትባላለህ ብሎ አውጥቶለታል። ይህ ከታላቁ ቅዱስ ጴጥሮስ ቀድሞ የተጠራው ሃዋርያ የመጀመሪያ የስብከት ስራው የነበረው በፍልስጤም ነበር ።

መልመጃ

1. በጠባዩ እና በቅልጥፍናው የታወቀው ልጅ ስም ማን ይባላል?
2. ጳጳሱ ጊልስን መከታተል ያልቻሉት በምን ምክንያት ነው?
3. ጊልስን ጓደኞቹ ከከተማ የጠፉት በምን ምክንያት ነው?

4. ጊልስ ቅዱስ የሃንስን ሲያይ ምን አደረገ
5. መጀመሪያ የተመረጠው ሃዋርያ ማን ነው ?
6. የእንድርያስ ሃገረ ስብከት የት ነው ?

ክፍለ ትምህርት 10

መግቢያ ጥያቄዎች (ያለፈውን ክፍለ ትምህርት ከከለሱ በኋላ)

1. ቤተ መንግስት ማለት ምን ማለት ነው?

ቅዱስ ቶማስ

በህንድ ሀገር ውስጥ ማላበር በምትባል ቦታ ጎንደፓርሽ የሚባል ንጉስ ነበር ይህ ንጉስ በኢየሩሳሌም ስላለው የሰሎሞን ቤተ መንግስት ዝና ይስማ ነበርና ያን የመሰለ ቤተመቅደስ ለመስራት ይመኝ ነበር። ሰለዚህ ነጋዴዎች በየሀገሩ ሲጓዙ የታወቀ ግንበኛ እንዲያመጡለት አዟቸው ነበር።

ይህን መልእክት ከሰሙት ነጋዴዎች መካካል አንዱ ወደ ፐርሻያ ወረደ ቅዱስ ቶማስ ወደ ህንድ ተጉዞ ወንጌልን ለመሰበክ መንገድ ሲፈልግ ከዚያ ነጋዴ ጋር ተገናኝተው ነገዴው የቶማስን ከኢየሩሳሌም መምጣት ሲሰማ የግንበኝነት ሙያ ይችል እንደሆን ጠየቀው ቶማስ በእየሩሳሌም በነበረበት ጊዜ ህንፃ በማነፅ ኦሮውን ይደግፍ እንደነበር ለነጋዴው መለሠለት።

ነጋዴው በዚህ አጋጣሚ እጅግ ተደስቶ ቶማስን ወደ ህንድ ማላበር ወስደው ንጉሡም የቶማስን ሙያ ሲሰማ ነፍሱአልቀረለትም ንጉስ ከታክሽሊለ ከተማ አጠገብ ወደ ሚገኘው ሜዳ ቶማስን ወሰደውና በጫካ የተሞላውን ሜዳ እያሳየ ቤተ መንግስቱ የሚተከልበትን ቦታ አመለከተው ቅዱስ ቶማስ የቤተመንግስቱን ዕቅድ ሲነግረው ንጉስ ጎንደፓረስ ተሠርቶ እስከሚያየው ቸኮለ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ንጉሡ ለሠራተኛ መቅጠሪያ፣ ለድንጋይና እብና በረድ፣ ለብርና ለወርቅ፣ ለብረትና እንጨት መግዣ እያለ ለቅዱስ ቶማስ ያለ የሌለውን ገንዘብ ይልክለት ጀመር። ቅዱስ ቶማስ ግን ገንዘቡን ለተቸገሩ ሠዎች ምግብ፣ ልብስ እና መጠለያ ይገዛበት ነበር በዚያውም ወንጌልን ይሠብክ ነበር።

ለቤተ መንግስቱ የተመደበው ገንዘብ እና ጊዜ እንደተጠናቀቀ ንጉሡ ቤተ መንግስቱን ሊጎበኝ መጣ። ንጉሡም ቤተ መንግስቱን ሲያጣ አንድ በዚያ የሚያልፍ መንገደኛን ጠራና ቶማስ የታለ/ ብሎ አፈጠጠበት። መንገደኛውም ቶማስ የተራቡትን እያበላ የተጠሙትን እያጠጣ፣ የታረዙትን እያለበሰ በድኾች መንደር ይገኛል አለው።

“እሱስ ባልከፋ ታዲያ የሠራልኝ ቤተ መንግስት የታለ? ብሎ የጠቀው።

“በድንጋይ የተሠራ ቤተ መንግስት ላያዩ ይችላሉ ጌታዬ ነገር ግን ህዝብዎ ገፅታ ላይ ደስታና ፈገግታ ማንበብ ይችላሉ አለው። መንገደኛው

በዚህ ጊዜ ንጉሡ ያ ሁሉ ገንዘብ እንደባከነበት መጠርጠር ጀመረ ወዲያው ወታደሮቹ ቶማስን ፍለጋ አካባቢውን አጥለቀለቁት።

ቅዱስ ቶማስ ተይዞ እንደመጣ "ቤተ መንግስቱን ለምን አልሠራህልኝም? አለው ንጉሡ።"

"ሠርቻለሁ ጌታዬ" ቶማስ መለሠ።

"የታለ? ጫካው እንኳን መች ተነሳ"

"እርግጥ በምድር ላይ የድንጋይ ቤተ መንግስት ላያዩ ይችላሉ እኔ ግን በሰማይ ላይ ቤተ መንግስት ሠርቼልዎታለሁ" አለው። ቶማስ ያን ጊዜ ንጉሡ ተቆጣ። ቶማስን እጅ እግሩን እየቆራረጡ እንዲያሠቃዩት አዝዘ መጎኒ አወረደው።

በዚች ሌሊት የንጉሡ ወንድም የሆነው ልዑል ጋድ በድንገተኛ በሽታ መጣደፍ ጀመረ። ሊነጋጋ ሲልም ነፍሱ ወጣች።

የጋድ ነፍስ በመላዕክት ታጅባ ወደ ሰማያት ወጣች። ካጀቧት ቅዱሣን መላዕክት አንዱ ብዙ አብያተ መንግስታትን እያሣያት ትኖረበት ዘንድ ደስ ያለሽን ምረጪ። አላት። የጋድ ነፍስም በአብያተ መንግስታቱ መካከል የሚታየውን የሚያምር ቤተ መንግስት መረጠች። መልዐኩም "ይህ ቤተ መንግስት ያንቺ አይደለም፣ ቶማስ ለንጉስ ጎንዶፓረስ የሠራለት ሰማያዊ ቤተ መንግስት ነው። አላት። በዚህች ሰዓት የልዑል ጋድ ነፍስ ከሥጋው ጋር ተዋሐደች።

ጋድ ሊቀብሩት በተሠበሰቡት ሠዎች መካከል ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ሠው ተንቀሣቀሠ። ከዚያም አፈፍ ብሎ ተነሣ። ልዑል ጋድ በዚያች ቅፅት የተመለከተውን ሁሉ ለንጉስ ጎንደፓረስና ለተሠበሠቡት ሁሉ ነገራቸው።

ንጉሡ ይህንን ሲሰማ በቶማስ ላይ በሠራው ግፍ ሁሉ አዘነ ተፀፀተም። ያሠበው ቤተ መንግስት መሠራቱን ሲሰማ ቶማስን ከወህኒ አወጣው። እርሱና ቤተሠቡም በክርስቶስ አምነው ተጠመቁ።


ሐዋርያው ናትናኤል

ሃዋርያው ስምኦን ለህገ ኦሪት ቀናተኛ የነበረ ሰው ነው ። ለህገ ኦሪት ይቀና ና ይቆረቆር ስለነበር ቀናተኛ ተባለ ። ሃገሩ ቃና ነው ። ለሐዋርያነት ይዞት የመጣው ፊሊጶስ የተባለው ሐዋርያ ነው። ስምኦን ሌላ ስሙ ናትናኤል ነው። ጌታችን በተወለደበት ዘመን ሄሮድስ ህጻናቱን ሲያስፈጃቸው እናቱ የበለስ ቅጠል ሸፍና አስመልጣው ስለነበር ጌታ ገና ሲመጣ አውቅሃለው አለው። እርሱም የት በማለት ጠየቀው። ጌታም ከበለስ በታች ተኝተህ ሳለህ አውቅሃለው ብሎ ያለፈ ህይወቱን ነግሮታል ከአስራ ሁለቱ ሃዋርያ አንዱ ሆኖ የክርስቶስን ወንጌል ሰብኳል።

መልመጃ

1. ንጉሱ ቤተ መንግስት መስራት የፈለገው ለምንድነው?
2. ቶማስ የንጉሱን ገንዘብ ምን አደረገበት?
3. ቶማስ ለንጉሱ ቤተመንግስት የሰራለት የት ነው?
4. የንጉሱ ቤተ መንግስት በሰማይ መኖሩ በምን ታወቀ?
5. ናትናኤልን ይዞት የመጣው ማነው?
6. ከበለስ በታች ሳለህ አውቅሃለው ያለው ማነው?

ክፍለ ትምህርት **11**



ቅዱስ ማቴዎስ

ቅዱስ ማቴዎስ በፍልስጤም ሀገር ሲያስተምር፣ ድውያንን ሲፈውስ አጋንንትን ሲያወጣ በማየታቸው የሃገሩ ሰዎች ወደ እስር ቤት ጣሉት። በእስር ቤት ውስጥም ከአንድ እስረኛ ጋር ተዋወቀ ይህ ሠው ሁልጊዜ ሀዘንና ትካዜ ያበዛ ነበር። ቅዱስ ማቴዎስም ጠጋ ብሎ እያጽናና ምን እንደሆነ ጠየቀው እርሱም ጌታዬ ባለፀጋ ነው። እኔም በመርከቡ እየተመላለስኩ እነግድለት ነበር። ባለፈው ሰሞን ግን ከንግዴ ስመለስ አልቀናኝም። ማዕበል ተነስቶ መርከቤ ከነእቃዋ ሰጠመች፣ ገንዘቤን ባህር በላው። እኔም በስንት መከራ ተርፌ መጣሁና ለጌታዬ የሆነውን ሁሉ ነገርኩት። እርሱ ግን በደረሠብኝ ከማዘንና በመትረፌም ከመደሠት ይልቅ መርከቡን በማስጠሜ ተበሳጭቶ ለእስር ዳረገኝ" አለው።

ቅዱስ ማቴዎስም "አይዞህ ከጥቂት ቀናት በኋላ ይፈታሃል" በማለት ማንም ተናግሮት እርሱም አስቦት የማያውቅ ነገር ተናገረው።

"ጌታህ ሊቀጣህ ይመጣል። በዚህ ጊዜ እባክህ መርከብህ ከባህር ወጥቷልና ላምጣው በለው ወደ ባህሩ ስትወርድ መርከብህን ታገኘዋለህ" በማለት አፅናናው።

ቅዱስ ማቴዎስም የተናገረው አልቀረም ከጥቂት ቀናት በኋላ ያ ባለ ፀጋ ሊቀጣው አገልጋዩን ጠራው። እርሱም እንዲታገሠውና ጊዜ እንዲሠጠው ለመነው። አገልጋዩ ወደ ባህር ወረደ መርከቧ ከባህር ላይ ከነሙሉ ሀብቱ ትንሣፈፋለች። እየቀዘፉ አምጥቶ ለባለፀጋው የነገደውን ሁሉ አስረከበው። ባለ ፀጋውም የሆነውን ሁሉ እንዲነግረው አገልጋዮን ጠየቀው። አገልጋዩም "የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዝሙር የሆነ ማቴዎስ መርከቤን እንደማገኝ ነገረኝ። እንዳለውም አገኘሁ" ሲል መለሰለት። "ለመሆኑ የት ይገኛል" አለው ባለፀጋው "በእሥር ቤት ውስጥ ወንጌልን እየሰበከ ይገኛል" ብሎ መለሰለት።

ያ ባለፀጋ ማቴዎስን አስጠርቶ ክርስትናን በመማር አምኖ ተጠመቀ። ቤተሰቡም ተጠመቁ። ወሬውም በከተማው ሁሉ ተዳረሰ ይህን የሠሙት መኳንንትም ማቴዎስን ለንጉሱ ከሠሱት። ንጉሡም በመኳንንቱ ተመርቶ በማቴዎስ ላይ ሞት ፈረደበት። አንገቱንም ተሰይፎ አረፈ። ያ ባለ ፀጋም በድብቅ ወስዶ ቀበረው።

ቅዱስ ፊሊጶስ

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ባኮስ ኢየሩሳሌም ደርሶ ሲመለስ በሰረገላ ላይ ተቀምጦ የነቢዩ ኢሳይያስን መጽሃፍ እያነበበ ሲመጣ ፊሊጶስ የተባለው ሃዋርያ አግኝቶት ስለሚያነበው መጽሃፍ ጠየቀው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባም ባኮስም የሚያስተምረኝ መምህር ስለሌለ ዝም ብዬ ነው የማነበው በማለት ተናገረ። ወንጌልን እያስተማረውም ተጓዙ በኋላም ጃንደረባው በቃሉ ልቡ እንደተነካ በኢየሱስ ክርስቶስም ማመኑን አረጋግጦ።ወደ ባህርም ሲደርሱ ተጠምቆዋል።በጃንደረባው በኩል ሐዋሪያው ፊሊጶስ ለኢትዮጵያውያን ወንጌልን ሰብኮልናል። ይህ ሃዋሪያ ጌታችንን አብን አሳየንና ይበቃናል በማለት ጠይቆ ምስጢረ ስላሴን ገልጾለታል። ጌታም ሲመልስ እኔና አብ አንድ ነን በማለት የስልጣን አንድነታቸውን ገልጿል።

መልመጃ

1. ቅዱስ ማቴዎስ የተዋወቀው እስረኛ ስራው ምንድን ነው?
2. መርከበኛው የታሰረው ምን አድርጎ ነው?
3. መርከበኛው ከእስር የተፈታው እንዴት ነው?
4. ማቴዎስ ባለጸጋውን ክርስትናን በማስተማሩ ምን አገኘ
5. ፊሊጶስ ያጠመቀው ማንን ነው ?
6. ፊሊጶስ ጌታን የጠየቀው ጥያቄ ምንድነው ? ጌታችን ምን ብሎ መለሰለት ?

ክፍለ ትምህርት 12

<u>መግቢያ ጥያቄዎች (ያለፈውን ክፍለ ትምህርት ከከለሱ በኋላ)</u>

1. መሃን (መካን) ምንድነው?

<u>ቅዱስ ያዕቆብ</u>

በኢየሩሳሌም ከተማ ቴዮብስጣ የተባለች ደግ ሴት ትኖር ነበር። በልዋ አማንዮስ የሚባል ከአይሁድ ምሁራን ወገን የነበረ ሰው ነው። 20 ዓመት በትዳር ሲኖሩ ልጅ አልነበራቸውም። አንድ ቀን የቅዱስ ያዕቆብና ዝና ሰማችና ወደ እርሱ መጥታ። "እባክህ እግዚአብሔር ልጅ እንዲሠጠኝ ፀልይልኝ" ብላ ለመነችው።

ቅዱስ ያዕቆብም "አይዞሽ አትዘኝ እመኝ እንጂ ይደረግልሻል" ብሎ አፅናንቶ ወደ ቤቷ ሰደዳት።

ቅዱስ ያዕቆብ ይህን በነገራት በዓመቱ ወንድ ልጅ ወለደች። ወደ ቅዱስ ያዕቆብ ወስዳም አስባረከችው። ስትመለስም የሆነውን ሁሉ ለባሏ አጫወተችው። እርሱ ግን እጅግ ተበሳጨ። የክርስቲያኖች ኃይል እየጠነከረ ከሄደማ ያሠጋናል የሚል ሃሣብ ስለተቀረፀበት ለወቅቱ የኢየሩሳሌም ሊቀ ካህናት ለሐናንያ ነግሮ አይሁድን በማሣመፅ ምክንያት ፈጥረው ያዕቆብን አሠሩት።

ሊቀ ካህናቱ አይሁድን በቤተ መቅደሱ ዙሪያ ከሰበሰበ በኋላ ቅዱስ ያዕቆብን ወደ መቅደሱ ጫፍ አውጥቶ በዚህ ህዝብ ፊት ክርስቶን ከደህ አስተምር ሲል አዘዘው። እርሱ ግን እዚያው ቆሞ መስበኩን ቀጠለ። በዚህ የተናደዱት የአይሁድ አለቆች ያዕቆብን ከቤተ መቅደሱ ጫፍ ወረወሩት። ከሥር የተሠበሰቡት ደግሞ በድንጋይ ወግረው ገደሉት።

መልመጃ

1. ልጅ ያልነበራቸው ሰዎች እነማን ነበሩ?
2. አማንዮስ ያዕቆብን የከሰሰው ለምንድን ነው?
3. አይሁድ ያዕቆብን የገደሉት እንዴት ነው?

<u>ቅዱስ ማትያስ</u>

ቅዱስ ማትያስ እስኩቴስ ወደ ሚባል ሀገር ወንጌልን ሊሰብክ ተጓዘ። በዚ ሀገር ይኖሩ የነበሩ ሠዎች በጣም ጨካኞችና ክፉዎች ነበሩ። የሠው ስጋንም ይበሉ ነበር።፤

ቅዱስ ማትያስ በዚህ ሀገር ሲያስተምር እነዚህ ሰዎች ያዙት ዓይኑን አውጥተው እንደ አንበሳ ሣር ያበሉት ጀመር። ምክንያቱም የዚህ ሀገር ሰዎች ሰውን ከመብላታቸው በፊት ዓይኑን አጥፍተው ለ 40 ቀናት ያህል ሣር ማብላት ልማዳቸው ስለነበር ነው። ሐዋርያው ማትያስ ለ 40 ቀናት በእስር ቤት ተቀመጠ።

ነገር ግን ሣሩን ምንም ሣይቀምስ በፀሎት ነበር ቀናቱን ያሣለፈው። በ 40 ኛው ቀን ሣሩን ከፊቱ ተከምሮ ሲዘምር ቅዱስ እንድርያስ ከእግዚአብሔር ተልኮ በተዘጋው በር ገባ። በደስታና በናፍቆት ሰላምታ ከተሠጣጡ በኋላ "እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል አልካችኋለሁ የሚለው ቃል ዛሬ በአንተ ተፈፀመ" ሲል የጌታን ቃል አስታወሰው። ከእስር ቤትም ይዞት ወጣ። አብረውት በዚያው ታሥረው የነበሩ 123 ሰዎችም ወጡ። ይህንን ተዓምር ያዩት የሀገሪቱ ሰዎችም በትምህርቱ አምነው ተጠመቁ።

መልመጃ

1. በእስኩቴስ ሃገር የነበሩ ሰዎች እንደምን አይነት ነበሩ?
2. በተዘጋው በር ጉበቶ ቅዱስ ማቲያስን ያወጣው ማን ነበር?
3. ከ ቅዱስ ማቲያስ ጋር አብረው የወጡት ሰዎች ስንት ናቸው?
4. ቅዱስ ማትያስ ለስንት ቀን ነው የታሰረው?

ክፍለ ትምህርት 13

<u>መግቢያ ጥያቄዎች (ያለፈውን ክፍለ ትምህርት ከከለሱ በኋላ)</u>

1. ጠንቋይ ታውቃላችሁ? ምንድን ነው ስራው? እንዴት ይሸነፋል?

<u>ቅዱስ ታዴዎስ</u>

ቅዱስ ታዴዎስና ቅዱስ ጴጥሮስ ወደ ሶሪያ ሲጓዙ መንገድ ብዙ በመጓዛቸው ራባቸው። በከተማ አጠገብ ሲደርሱ አንድ ሽማግሌ ሲያርሱ አገኟቸው። ቅዱስ ጴጥሮስ እባክዎን የምንበላው ነገር ይስጡን ? በማለት ጠየቋቸው። እኒያም ሽማግሌ ደግ ስለነበሩ ከቤት እስካመጣላችሁ ድረስ በሬዎቼን ጠብቁልኝ ብለው ወደ መንደር ገቡ ።

ሁለቱም ሐዋርያት የገበሬውን ደግነት ተመልክተው ታዴዎስ ጠምዶ ሲያርስ ጴጥሮስ መዝራት ጀመረ። ገበሬው ምግብ ይዞ ሲመለስ የተዘራው በአንድ ቀን በቅሎ እሸት ይዞ ጠበቀው። ይህን ተዓምር የተመለከቱት ገበሬ ባዩት ተደንቀው እናንተ ከሰማይ የወረዳችሁ አማልክት ናችሁን? ብለው ጠየቋቸው።

እነርሱ ግን ለሽማግሌው ወንጌልን ነገሯቸው። ገበሬውም እሸቱን ወስደው ለሚስታቸው አሳዩአት። ለከተማው ሰዎችም ያዩትን ታሪክ ነገሩ።

ከዚህ በኋላ የከተማው መኳንንት ነገሩን በሰሙ ጊዜ ይህ ከ 12 ቱ አስማተኞች ወገን ሳይሆን አይቀርምና ወደ ከተማችን እንዳይገባ ምን እናድርግ ተባባሉ ። ከመካከላቸው አንዱ እነዚህ 12 ቱ አስማተኞች

ዝሙትን ይጸየፋሉና ዘማዊት ሴት በከተማችን በር እናቁም ብሎ ስለመከራቸው በከተማቸው በር ላይ የታወቀች ዘማዊት ሴት ራቁቷን አድርገው አቆሟት ።

ቅዱስታዴዎስ ቀን ገጠር ገጠሩን ሲያስተምር ውሎ ማታ ወደ ከተማው ሲመጣ ያቺ ዘማዊ ሴት በከተማው በር ቆማ አያት ያን ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ ። በዚህ ሰዓት ወደ አየር ወጥታ በነፋስ አውታር ተንጠለጠለች ።የሃገሩ ሰዎች እስኪገረሙ ድረስ ትጮህ ነበር። እርሱ ግን ወደ ከተማው ጉብዩ ወንጌልን መስበክ ቀጠለ ። ያቺን ሴት ከተንጠለጠለችበት አውርዶ አሳምኖ በማጥመቅ በቤትዋ የክርስቲያኖች ጉባኤ ተመስርቷል።

ወንጌላዊው ሉቃስ

ሃኪም ና ሰዓሊየነበረ ሰው ነው። ከእለታት አንድ ቀን ቀልዮጳ ከሚባል ወዳጁ ጋር ኤማሁስ ወደምትባል ከተማ እያወሩ ሲጓዙ አይሁድ ኢየሱስ ክርስቶስን የሰቀሉበት ሰሞን ነበረና ወሬያቸውም ይህ ነበር። በመካከልም አንድ ሰው ከእነርሱ ጋር ተቀላቅሎ መሄድ ጀመረ ። የሚነጋገሩትም ስለምን እንደሆነ ጠየቃቸው እነርሱም ለሃገሩ አዲስ ነህን አይሁድ ኢየሱስን ምን እንዳደረጉት አታውቅምን እርሱ ደግ መምህር ነበር ። አይሁድ ግን በቅናት ይህ ሰው በሰንበት የታመሙትን ፈወሰ ፣ ጎባጣውን አቀና ፣ አይናቸው የታወሩትን አበራላቸው ብለው በመስቀል ሰቅለው ገደሉት በማለት ነገሩት። እርሱም ብዙ ነገርን አስተማራቸው ። ኤማሁስ ሲደርሱም መሸቶ ነበርና እንግዳውን ሰው ከኛ ጋር እደር አሉት። ወደቤትም ይዘውት ገቡ በእራት ላይም ተቀምጠው ሳለ ባርኮ ሰጣቸው በተመገቡ ጊዜ አይናቸው ተከፈተ አብሮአቸው የነበረው ክርስቶስ ኢየሱስ እንደነበረ አወቁ። አይናቸው ተከፈተ ስንል ልቦናቸው ማስተዋል ጀመረ ማለታችን ነው። ትንሳኤውን ገለጠላቸው ። ከዚህ በኋላ ሉቃስ ወንጌልን ጽፎልናል።

ወንጌላዊው ቅዱስ ማርቆስ

ኢየሩሳሌም ውስጥ ክርስቲያኖች በቤቱ በጸሎት ይሰበሰቡ የነበረችው የማርያም ባውፍልያ ልጅ ነው።

ትውልዱ ዕብራዊ ሆኖ ቤተሰቦቹ ይኖሩ የነበሩ በሰሜን አፍሪካ ቀሬና በተባለችው በዛሬዋ ሊቢያ ምዕራባዊ ክፍል ነው። ነገር ግን ያደገው በኢየሩሳሌም ነው። ጌታችን ሲያስተምር ገና ልጅ ነበር ።

ይህ ሃዋርያ በርናባስ አጎቱ ነው። ከሃዋርያው ጳውሎስ ጋር አብሮ አስተምሮዋል። በተለይ የ ጴጥሮስ ተከታይና ተማሪ ስለነበረ ልጁ ይለዋል። ከ ጴጥሮስ የሰማውንና የተማረውን መሰረት በማድረግ ጽፎአል።

ወንጌላዊው ማርቆስ በጣኦት አምልኮ የሚታወቁትን የግብጻውያንን ባእድ አምልኮ በማጥፋት የእስክንድርያን ቤተክርስቲያን መስርቷል።

ለአለም የተረፉ ቅዱሳን አባቶችን ያፈራችው ቤተክርስቲያን የተመሰረተችሁ በእርሱ ነው።ክርስቲያኖችን በማስተማርና በማጽናናት ከኖረ በኋላ ጣኦት አምላኪዎች መሬት ለመሬት ጎትተውት ካሰቃዩት በኋላ በሰማእትነት ያረፈውም ሚያዚያ 30 ቀን ነው ።

መልመጃ

1. ቅዱስ ታዴዎስና ቅዱስ ጴጥሮስ ገበሬውን ምን ጠየቁት?
2. ቅዱስ ታዴዎስ ወደ ከተማው እንዳይመጣ ሰዎቹ ምን አደረጉ?
3. ቅዱስ ሉቃስ ስራው ምን አደረገ ?
4. ቅዱስ ማርቆስ እናቱ ማን ናት ?
5. ቅዱስ ማርቆስ የመሰረታት ቤተክርስቲያን ማናት?

ክፍለ ትምህርት **14**

መግቢያ ጥያቄዎች (ያለፈውን ክፍለ ትምህርት ከከለሱ በኋላ)

1. መጀመሪያ ሰማዕት የሆነው ማን ይመስላቹሃል?

ቅዱስ እስጢፋኖስ

እስጢፋኖስ ማለት በግሪክ ቋንቋ አክሊል ማለት ሲሆን አባቱ ስምኦን እናቱ ሃና ይባላሉ ። ትውልዱም ከነገደ ቢንያም ነው ። የተወለደው ሀኖስ በተባለ ስፍራ ነው። በዘመነ ሐዋርያት በማህበረ ምዕመናን መካከል በአረማውያንና በአይሁድ ሴቶች ጡብ የተነሳ መነቃቀፍ በመጀመሩ ምዕመናንን በሚገባ የሚያስተዳድሩ ሰባት ዲያቆናት ተሾሙ። ከእነዚህም አንዱ ቅዱስ እስጢፋኖስ ነበር። ቅዱስ እስጢፋኖስ የስድስቱ ዲያቆናት አለቃ(ሊቀ ዲያቆናት) በመሆን ምእመናንን ከማገልገል ባሻገር ድውያንን በመፈወስ ትምህርተ ወንጌልን በማስፋፋት የበረታ ነበር።

በገድሉ እንደ ተጻፈው ናዖስ የሚባል ጠንቋይ ወደ አንድ በሬ ሄዶ በጆሮው ሹክ ቢል በምትሃት ከሁለት ተከፈለ። ቅዱስ እስጢፋኖስም በተሰጠው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የሞተውን አንስቶ የተከፈለውን ገጥሞ ናዖስን ጠርተህው ና ብሎ

አዘዘው ። የበልዓም አህያ አንደበት አውጥታ እንደተናገረችው ያም በሬ እንደ ሰው እያወራ ጠንቋዩን ጠራው። ህዝቡም ቅዱስ እስጢፋኖስ ባደረገው ተዓምር እየተገረሙ አምነው ተጠመቁ። ይህም አይሁድ በቅንዓት በቅዱስ እስጢፋኖስ ላይ እንዲነሰብት አደረጋቸው። የውሸት ምስክር አቁመው በሸንጎው ከሰሱት ። እነርሱም ምሌክ የተባለ ጣኦት ያመልኩ ነበርና እግዚአብሄርን የምታመልኩ እየመሰላችሁ ጣኦት የምታመልኩ እያለ አይሁድን በሸንጎ ነቀፋቸው እነርሱም በንዴት ከከተማ አውጥተው በድንጋይ ሊወግሩት ፈለጉ። አውጥተው ሲደበድቡት እርሱ ግን ሰማያት ተከፍተው ኢየሱስ ክርስቶስን በአብ ቀኝ ቆሞ አየዋለው በማለት የሰማዩን ምስጢር ሲመለከት እነርሱ ግን የድንጋይ ውርጅብኝ ያወርዱበት ነበር። እርሱም የሚያደርጉትን እያውቁምና ይቅር በላቸው በማለት ጸልዮ በሰማዕትነት አረፈ ። ዛሬም ቤተክርስቲያን ጥር 1 ቀን ነው ። ቀዳሚ(የመጀመሪያው) ሰማእት ብላ ትጠራዋለች ።

ቅዱስ ጳውሎስ

በቀድሞ ስሙ ሳኦል ይባል ነበር ክርስቲያኖች እያሣደደ ይገድላቸው የነበረና ኃይለኛ ሰው ነበር። በአይሁድ እጅግ ይፈራ ነበር። አንድ ቀን ወደ ደማስቆ ክርስቲያኖችን ለማሣደድ ሠይፍ መዞ ሲሄድ በመንገድ እንደ መብረቅ ብልጭታ ታይቶት ከመሬት ወደቀ አይኑም ታወረ። ከዚህ በኋላ ድምፅ ከሠማይ ሣኦል ሣኦል ስለምን ታሣድደኛለህ የሚል መጣ እርሱም አንተ የማሣድድ ማነህ በማለት ጠየቀው እርሱም እኔ የናዝሬቱ ኢየሱስ ነኝ አለው። ሳኦልም ምን እንዳደርግ ትወዳለህ አለው እርሱም ከዚህ በኋላ ስምህ ጳውሎስ ይባላል አሁን ሃናንያ የሚባል ሠው አለ ወደ እርሱ ሂድና እርሱ ይጸልይልህ በማለት አዘዘው ሃናንያ ፀለየለት ከአይኑም እንደ ቅርፊት ወደቀ ከሃዋርያትም ጋር አስተዋወቀው ከዚህ ጊዜ ጀምሮ

ጳውሎስ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል መስበክ ጀመረ ከሃገር ወደ ሃገር እየተዘዋወረ ያስተምራል ድንኳን ይሠፋል እንዲህ እያደረገ ከአምላኩ ጋር በፀሎት እየተነጋገረ በመጨረሻ ኢየሱስ ክርስቶስ የተባለው ካደውና እንደ ድሮው ክርስቲያኖች ግደል ያለበለዚያ አንተ ትገድላለህ ተብሎ አንገቱን ለሠይፍ ሠጥቶ በሠማዕትነት አረፈ።

መልመጃ

1. ቅዱስ እስጢፋኖስ በሬውን ያደረገው ምንድነው
2. በድንጋይ ሲወግሩት ምን ብሎ ተናገረ?
3. የጳውሎስ የቀድሞ ስሙ ማን ይባላል ?
4. ለምን ታሳድደኛለህ ያለው ማን ነው ?
5. ለጳውሎስ የጸለየለት ሰው ማን ይባላል?
6. የጳውሎስ ስራው ምንድን ነው?